ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ

The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of science &hiegher Education
Debre Markos University

የጨረታ ማስታወቂያ

ደ/ማ/ዩ ብ/ግ/ጨ/40/2012

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ለ2013 የበጀት ዓመት ለተማሪዎች ምግብ አገልግሎት የሚውል ማለትም ፡-
ጥቅል 1. ፈሳሽ ዘይት
ጥቅል 2.ቀይ ሽንኩርት እና ድንች ለ1 ዓመት የሚቆይ በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡
ስለሆነም ፡-

1. በዘመኑ እና በዘርፉ የታደሰ የንግድ ስራ ፈቃድ እና የግብር ከፋይነት የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ እና የግዥ መጠኑ ብር200,000.00/ሁለት መቶ ሽህ ብር/እና በላይ ከሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆኑእና የተመዝጋቢነት ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፤
2. አሸናፊው ድርጅት ያሸነፈባቸውን እቃዎች በሚሰጠው ፕሮግራም መሰረት ውል በመያዝ ደ/ማ/ዩ ንብረት ክፍል ገቢ ያደርጋል፡፡
3. ለጨረታ ማስከበሪያ የሚሆን ለጥቅል1 ብር 30,000.00 (ሰላሳ ሽህ ብር) እና ለጥቅል 2 ብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሽህ ብር) በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ስም አሰርቶ ማቅረብ የሚችል ወይም በጥቃቅን የተደራጁ ከአደራጃቸው የመንግስት መ/ቤት ከላይ የተገለጸውን የገንዘብ መጠን የሚገልጽ የዋስትና ደብዳቤ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ስም በማሰራት ማቅረብ የሚችሉ፡፡
4. ከላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ተጫራቾች ሁሉ የጨረታ ዶክመንቱን ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ አስተዳደር ህንፃ ቁጥር 27 ቢሮ ቁጥር 10 ወይንም አዲስ አበባ 4 ኪሎ ከቅድስት ማሪያም ቤክርስቲያን ወረድ ብሎ ሮሚና ካፌ ላይ 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 7 ከሚገኘው ቢሮአችን ማስታወቂያው በአዲስ ዘመን ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ 15 ተከታታይ ቀናት የማይመለስ ብር 200.00/ሁለት መቶ ብር / በመክፈል መግዛት ይችላሉ፡፡
5. የጨረታውን ዶክመንት አስተማማኝ በሆነ ማጣበቂያ በታሸገ ፖስታ በማድረግና በፖስታ ላይ የአሰሪ መስሪያ ቤቱንና የድርጅቱን መሉ ስምና አድራሻ በመጻፍ ፊርማና ማህተም በማድረግ ማቅረብ አለባቸው፡፡
6. የጨረታውን ፋይናሽያል ኦርጅናል እና ኮፒ ዶክመንት በተለያየ ፖስታ በማሸግ ማቅረብ አለበት፡፡
7. አሸናፊው ድርጅት አሸናፊነቱ በተገለፀለት ከ7 ተከታታይ የስራ ቀናት በኋላ ከ8ኛ ቀን ጀምሮ በተከታታይ 8 የስራ ቀናት ውስጥ በግንባር ቀርቦ አሸናፊ የሆነበትን ጠቅላላ ዋጋ 10% የውል ማስከበሪያ በማስያዝ ውል መያዝ የሚችል መሆን አለበት፡፡
8. ተወዳዳሪዎች የጨረታ ሰነዱን በአግባቡ በመሙላትና በማሸግ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ህንፃ ቁጥር 27 ቢሮ ቁጥር 10 ድረስ በመቅረብ ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ከተከታታይ 15 ቀናት በኋላ በ16 ኛው ቀን ከጠዋቱ 3:59 ድረስ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ሲኖርባቸው ጨረታው በዚሁ እለት ከጠዋቱ 4:00 ሰዓት ላይ ተዘግቶ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት 4:30 ላይ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ህንፃ ቁጥር 27 ቢሮ ቁጥር 10 ውስጥ ይከፈታል፤ነገር ግን የጨረታ መዝጊያ እና መክፈቻ ቀኑ የበአል ቀን ከሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን ይሆናል ፡፡
ሆኖም ተጫራቾች በጨረታው ላይ መገኘት ካልቻሉ መስፈርቱን እስካሟሉ ድረስ በጨረታው ላይ ያልተገኙ ተጫራቾች ፖስታ ጨምሮ በእለቱ ይከፈታል፡፡

የበለጠ መረጃ ለማግኘት በስልክ ቁጥር 058 771 66 91/058/178 00 37/ ደውለው መጠየቅ ይችላሉ፡፡

ዩኒቨርሲቲው ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው

ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ